# <u>በማር የተለወሰ መርዝ</u>

(ለአብርሃም ያየህ «የጥላቻ ፖለቲካ» በሚል ርእስ *ኢትዮጵያ ዛሬ ድህረ ገጽ* ለወጣ ጽሁፍ የተሰጠ መልስ)

«የጥላቻ ፖለቲካ» በሚል አቶ አብርሃም ያየህ የጻፈዉን በማር የተለወሰ መርዝ ያለበትን ደብዳቤ በቅርቡ *ኢትዮጵያ ዛሬ ድህረ ገጽ* ላይ አነበብን። አቶ አብርሃም ያየህ ይህንን ሲጽፍ ሁለት አላማ አለዉ። አንዱ አላማዉ የትግራይ ህዝብ ተቆርቋሪ በመምሰል ከመለሰ ዜናዊ ምህረት ልመና ሲሆን ሁለተኛዉ አላማዉ ደግሞ አማራዉን ህዝብ ጸረ ትግራይ አድርጎ በማቅረብ ሁላችንም በአማራዉ ላይ እንንዝመት የሚል ስዉር መልእክት ማስተላለፉ ነዉ። አቶ አብርሃም ሁለቱም አላማወች አይሰሩም። የመጀመሪያዉ አላማ የማይሰራበት ምክንያት መለሰ ዜናዊን ምን እያልክ ስሙን ስታጠፋዉ እንደነበር ማንም ያዉቃል። አንተ አይደለህ እንዴ የወያኔ መሪዎች ከኢትዮጵያ ይልቅ ኤርትራን ይወዳሉ ብለህ የነገርከን። አንተ ነበርክ የወያኔ መሪዎች አላማቸዉ ትግራይን ገንጥለዉ ከኤርትራ ለመቀላቀል ነዉ ብለህ የነገርከንን ረሳህዉ እንዴ? ታዲያ መለስን እያወቅከዉ እንዴት አድርጎ ይምርሀል።

ሁለተኛዉ አላማህ የማይሰራበት ምክንያት ደግሞ አንተ በትግራይ ህዝብ የተተፋህ ሰዉ ነህ። ምክንያቱም መያዣ መጨበጫ የለለህ ሰዉ ነህ። አንድ ጊዜ ትግራይ ሌላ ጊዜ ኤርትራ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከደርግ ጋር እያልክ የምትገለባበጥ አቋም የሌለህ ሰዉ ነህ። የአንዳንድ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዉንን ስም እየጠቀስክ ጸረ ትግራይ ናቸዉ ለማለት ሞክረሃል። እስኪ አንድ አንዶችን እንመልከት። ታማኝ በየነን ጠቅሰሃል። ታማኝ ትግራይ በሻቢያ በተጠቃች ጊዜ አንተና መሰሎችህ ከአልሄዳችሁበት ጦር ግንባር ድረስ በመሄድ የኢትዮጵያን ሰራዊት የአበረታታ አገር ወዳድ ነዉ። አቶ ምርጫዉን አንስተህ ጸረ ትግራይ አድርገህ ለመሳል ሞክረሃል ይህም ዉሸት ነዉ። እኛ እስከ ተክታተልነው ድረስ አቶ ምርጫዉ በኢትዮጵያዉነት ሬድዮ ሁልጊዜ የሚያስተላልፈዉ መልክት የወያኔ መሪዎች የትግራይን ህዝብ አይወክሉም በትግራይ ህዝብ ስም የሚነግዱ ወንበዴወች ናቸዉ ነዉ የሚለዉ። አቶ አብርሃም በዚህ ላይ ችግር ካለብህ ንገረን ያለዚያ ግን ልታምታታን አትሞክር ያ ጊዜ አልፋል። ሌሎችን ሰዎችም ስም ጠርተህ ፕሮፌሰር ጥላሁን ይልማ የአማራ ብሄር ተወላጅ ዶ/ር አሰፋ ነጋሽ የአማራ ብሄር ተወላጅ ብለህ ወንጅለሃል። የአንተ መልእክት አማራን እናጥፋ ነዉ። ምነዉ ዛሬ ደርሰህ ጸረ አማራ ሆንክ? ወያኔ አሳደደኝ እያልክ ካምፓላ ሆነህ ስትጣራ ለአንተ የጮሁትን አማሮች ረሳኻቸዉ እንዴ?

<u>ዉድ ኢትዮጵያዉያን</u> አቶ አብርሃም ያየህ አንቀጽ 39 ተጠቅሜ መገንጠልን እመርጣለሁ ይለናል። ኢትዮጵያ በአፍንጫየ ትዉጣ ይለናል። ይህ አደገኛ አባባል ነዉ። ማወቅ ያለብን ይህ ሀሳብ የአቶ አብርሃም ያየህ የብቻዉ አይደለም። ከመሰሎቹ ጋር የዶለቱት ይመስለል። ሲገነጠሉስ እኛንስ እንዴት አድርገዉን ነዉ የሚሄዱት? በከፍተኛ አደጋ ላይ እንገኛለን። <u>ዉድ ኢትዮጵያዉያን</u> ከዚህ የበለጠ መረጃ ማግኘት አያስፈልገነም። አገራችን እንዳትፈርስ ህዝባችን ላይ እልቂት እንዳይደርስ ነቅተን መጠበቅ ይገባናል። ለአቶ አብርሃም ያየህና ለመሰሎቹ ማስተላለፍ የምንፈልገዉ መልክት ቢኖር አንቀጽ 39 የኢትዮጵያ ህዝብ በድምፁ ያስቀመጠዉ አንቀጽ ሳይሆን የወያኔ ባለስልጣኖች በመሳሪያ ሀይል ያስቀመጡት አንቀጽ መሆኑንና ህዝባዊ መንግስት ኢትዮጵያ ዉስጥ ሲመጣ አንቀጽ 39 የት እንደምትወረወር ለማየት እድሜ ይስጣችሁ ነዉ።

<u>*ለኢትዮጵያ ዛሬ ድህረ ገጽ አዘጋጆች*</u> አገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በብዙ ችግር ተወጥራ በምትገኝበት ጊዜ ስንት አንገብጋቢ ጉዳይ እያለ የአቶ አብርሃም ያየህን በማር የተለወሰ መርዝ ያለበትን 16 ገፅ ደብዳቤ አስነበባችሁን። አቶ አብርሃም ያየህ አሞኝቷችኋል። ይህኔ ከመሰሎቹ ጋር ሆኖ እነዚህን አድጊዎች ተጫወትኩባቸዉ ብሎ እየሳቀባችሁ ነዉ። እናንተ የአያችሁት «የጥላቻ ፖለቲካ» የሚለዉን አርእስት ነዉ ጠቅላላ መልእክቱ ግን እኛ እስካልገዛናችሁ ድረስ አገሩም አገር ሰዉም ሰዉ አይሆንም ነዉ የሚለዉ። አቶ አብርሃም ያየህን አንድ ጊዜ አሞኝቷችኋል። ወደፊት ግን ለኢትዮጵያ

ህዝብ ምን ያህል ጠቃሚነት አለዉ ብላችሁ መርምራችሁ እንደምታቀርቡና ስዉር አጀንዳ ለአላቸዉ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች መጠቀሚያ እንደማትሆኑ እንተማመናለን።

አንቀጽ 39 ይከሽፋል።
ስዉር አጀንዳ ለአላቸዉ ግለሰቦችና ድርጅቶች እንጠንቀቅ።
ኢትዮጵያና ኢትዮጵዊነት ለዘላለም ይኖራሉ።

ከአገር ወዳድ ኢትዮጵያዉያን ቶሮንቶ ካናዳ።

EthioLion.Com